# ወይ ነዶ! (ኖኅተብርሃን ጌጡ)

**November 29, 2017**

*ለካስ አንዲህ ነዉ መማር፤*
*መፈላሰፍ፤ መምጠቅ ጠፈር፤*
*አዲስ ግኝት በትርጉም መፍጠር፡*
*ዶክትሬትን መሥራት በሀገር ቀመር።*
*የሀገርን ሥም ማስጠራት ባለም፤*
*ከመጽሐፍ ቅዱስ አሰርዞ ማጻፍ በቀይ ቀለም።*
*እንዲህ ነዉ ምሁር ሊቀ ጠበብት መሆን፤*
*መምጠቅ በጥበብ፤ በትርጉም መካን።*
*ኃበ እግዚአብሔር እደዊኃ፤*
*ታበጽህ ኢትዮጵያ፤*
*የሚለዉን አሰርዞ ሲተካዉ በኩሽ፤*
*እንዲህ ዓይነት ምሁር የት ተገኝቶ በምድርሽ፤*
*ዉኃ ሆኖ ሳይቀር እንኩዋንስ ተወለደልሽ፤*
*የመመረቂያ ዶክትሬቱንም እንኩዋንስ ባንች ሰራብሽ፤*
*ባይወለድ ኖሮ፤ እንዲህ ዓይነቱ አኩሪ ልጅሽ፤*
*ከአፅናፍ አፅናፍ መች ይጠፉ ነበር፤ የተከበረዉ የመፅሐፍ ቅዱስ ሥምሽ፤*
*ሳይታወቅ ይቀር ነበር፤ ዳግም ጥምቀትሽ፤*
*በአዲሱ የክርስትና ሥምሽ መንቆለጳጰስሽ፤*
*መጠራትሽ፤ ተብለሽ ኩሽ፤*
*በጥራት መተርጎምሽ፤*
*ተጣሞ ኖሮ ሥምሽ፤ የኃበጠው ተቃናልሽ፤*
*እንዲህ ዓይነት ልጅ አንኩዋንስ አፈራ ማህጸንሽ።*
*እናም እንኩዋንስ ተወለደልን፤*
*ዶክተሩም ይደግ ይመንደግልን፤ ለሌላም ማዕረግ ይብቃልን፤*
*የሀገር ሥም እንዲህ በክርስቲያኖቹ እንዲያስጠራልን፤*
*ባጭር እንዳይቀር እባካችሁ ጸልዩልን።*
*እንዲህ ዓይነት ልጅ አይወለድምና ዳግም፤*
*ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚያጠፉ የሀገሩን ሥም።*

## ኢትዮጵያ ዝም አትበይ! እባክሽ ተናገሪ!

*ኢትዮጵያ እባክሽ ተናገሪ!  ምንድነዉ ችግርሽ?*
*ወልደሽ ያሳደግሻቸዉ ልጆችሽ እንዲህ የሚዘምቱብሽ፤*
*አንደኛዉን አስተምረሽ፤አሳድገሽ፤*
*በዓፄዉ ዘመን ጠቅላይ ኢቃቤ ሕግ አድርሰሽ፤*
*የሌላ አገር ሰዉ ሆኖ፤ እንድትፈራርሽ ፈረደብሽ።*
*ሌላኛዉ ዘመተ በታሪክሽ፤*
*መቶ ዓመት ይበቃታል ብሎ፤ ወርድና ቁመት ሰጥቶ በየነብሽ፤*
*የነፃነት ዓርማሽን፤ ጨርቅ ነዉ ብሎ ሞገተሽ፤*
*ከመሞገትም አልፎ ተዘባበተብሽ፤*
*በመጨረሻዉ ሰዓት ተጠቅልሎ ሊያሽልብልሽ፤*

*ባፈዘባት ባንዲራ በጨርቁዋ ሊሸኙልሽ፤*
*ይህ ሁሉ ችግር ከምን የመጣ ነዉ ትያለሽ?*

**ተናገሪ ካልከኝማ!**

*ባትጠይቀኝ ጥሩ ነበር፤*
*ሆድ ይፍጀዉ ብዬ ትቼዉ እየኖርኩ ነበር፤*
*ከጠየከኝማ መልሱንም መስማት ከፈለክ፤*
*እስኪ ሳላንዛዛ ትንሽ ልዘክዝክ።*
*በሚታየዉ ችግር ልጆቼን መዉቀስ አልችልም፤*
*እነሱ የሚያዉቁት ምንም ነገር የለም፤*
*እንዲህ ኣድርጌም አላሳደኩዋቸዉም፤*
*ጥፋቱ ያለዉ ከእኔዉ ከእራሴ ነዉ፤*
*ሳልንበረከክ ለቅኝ ፍዛት፤*
*ለዘመናት መኖሬ በነፃነት፤*
*ተደምሮ ከሃይማኖቴም ጋር ጥንታዊነት፤*
*አልተመቻቸዉም በሁዋላ ለይ ለመጡት።*
*እናም ምንም የማያዉቁትን ልጆቼን፤*
*በማህጸኔ አቅፌያቸዉ የኖሩትን፤*
*በጡቴም ያሳደኩዋቸዉን።*
*መርዝ ያጠጡ፤ መርፌ እየወጉ ላኩዋቸዉ፤*
*እንዲዘምቱላቸዉ በእናታቸዉ።*
*ልጆቼም ተወናበዱና፤*
*ለእነ ሥም ኣይጠሬ ተላላኪ ሆኑና፤*
*ጥብቅናም ቆሙላቸዉና።*
*መሣሪያ ሆነዉ የጌቶቻቸዉን ትዕዛዝ ፈጸሙ፤*
*ይህ ይመስለኛል የሚዘመትብኝ ትርጉሙ።*
*ከዚህ የተረፈዉን፤*
*ጠይቅ ተመራማሪ ተርጉዋሚ ልጆቼን፤*
*ለአሁኑ ዘመኑ፤ ለአሁኑ ሰዓት ያበቁኝን።*

(ኖኅተብርሃን ጌጡ)